WANotify.org/Amharic

# WA NOTIFY እንዴት እንደሚሰራ

Washington Exposure Notifications (WA Notify) ወሳኝ የሆነ አዲስ መሳሪያ ሲሆን የ COVID-19 ስርጭትን ለማስቆም የሚረዳ ነው። ልክ የፊት ጭምብል እንደማድረግ፣ እንደመራራቅ እና ስብስቦችን እንደመቀነስ፣ WA Notify ቀላል የሆነ ማህበረሰባችንን የሚጠብቅ መሳሪያ ነው።

WA Notify በስማርት ስልኮች የሚሰራ ሲሆን፣ ምንም አይነት የግል መረጃን ሳያጋራ ተጠቃሚዎች ለ COVID-19 ተጋላጭ ሆነው እንደሆነ የሚያሳውቅ ነው። **ሙሉ በሙሉ ግላዊ ሲሆን ማን እንደሆኑ የማያውቅ እና የት እንደሄዱ ክትትል የማያደርግ ነው።**

የተጋላጭነት ማሳወቂያዎችን የሚጠቀሙ ሰዎች በበዙ ቁጥር ጥቅሙ ይጨምራል። ዋሺንግተን ስቴት ውስጥ ያሉ የመረጃ ሞዴሎች WA Notify የሚጠቀሙ ሰዎች ትንሽ ቢሆኑም እንኳን መበከሎችን እና ሞቶችን ይቀንሳሉ።

## WA NOTIFY ን ስልክዎ ላይ ይጨምሩ

**iPhone ዎ ላይ:**

1. ወደ ቅንብሮች ይሂዱ
2. ወደ ተጋላጭነት ማሳወቂያዎች ያንሸራቱ
3. “Turn On Exposure Notifications” ላይ ጠቅ ያድርጉ
4. United States ን ይምረጡ
5. Washington ን ይምረጡ

**Android ላይ:**

1. በ Android ስልክ ላይ ወደ Google Play Store ይሂዱ
2. መተግበሪያውን በቀላሉ ለማግኘት WA Exposure Notifications ብለው ይፈልጉ
3. የ Washington Exposure Notifications መተግበሪያን ያውርዱ

## WA NOTIFY ን አንድ ጊዜ በስልክዎ ላይ ከጨመሩ በኋላ

### የ COVID-19 ስርጭትን ለመከላከል እንዴት እንደሚሰራ።

**1**




WA Notify በስልካቸው ላይ የሚጠቀሙ ሁለት ሰዎች ሲቀራረቡ፣ ስልኮቻቸው Bluetoothን በመጠቀም ዘፈቀዳዊ ኮዶችን ይቀያየራሉ። **ኮዱ ሙሉ በሙሉ ማንነትን የማያሳውቅ ሲሆን፣ ምንም አይነት የቦታ ክትትል ወይም የግላዊ መረጃ ልውውጥ አያደርግም።**

**2**




ዋሺንግተን ውስጥ ያለ አንድ ሰው ፖዜቲቭ ውጤት ሲኖረው እና ማህበረበሰብ ጤና ሲያገኘው፣ WA Notify ካላቸው ይጠየቁ እና ማረጋገጫ ኮድ ይሰጣቸዋል።

**3**



አፖዜቲቭ ውጤት የሚኖረው ሰው ማረጋገጫ ኮዱን WA Notify ውስጥ ያስገባዋል። ይህ በራስ ፈቃድ ላይ የሚሰረት ነው።

**4**



WA Notify ያለው እና ፖዜቲቭ ውጤት ላለው ሰው ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ለረጅም ጊዜ ቅርብ የነበረ ሰው ማንነትን የማሳያሳውቅ ለ COVID-19 ተጋላጭ ሆኖ ሊሆን እንደሚችል የሚያሳውቅ ማሳወቂያ ይደርሰዋል።

**5**




ማሳወቂያዎች ራስዎን እና ሌሎችን ለመጠበቅ ምን ማድረግ እንዳለብዎ የሚያሳውቅ ማስፈንጠሪያ አላቸው። ማን ፖዜቲቭ ውጤት እንዳለው ወይም ተጋላጭነቱ የት ተፈጥሮ ሊሆን እንደሚችል የሚያሳውቅ ምንም አይነት መረጃ አይይዙም።